በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ

Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

*የተሰጠ መግለጫ*

***ቀን፡ ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም***

## ***<u>የመምህራን መብት ሊከበር የሚችለው ሕዝባዊ ሥርዓት ሲቋቋም ብቻ ነው!!</u>***

*የኢትዮጵያ መምህራን ጎሳን መሰረት ባደረገው በወያኔ ዘረኛ ስርዓት ላለፉት 26 ዓመታት በእጅጉ ተጠቂ እንደሆኑ ይታወቃል። መምህራን ወያኔ በሰፋው የጎሳ ኮሮጆ ውስጥ ለመግባት ፍቃደኞች ስላልሆኑ ብቻ ለእኩል የትምህርት ደረጃ እኩል ክፍያ፣ የትምህርት እድል ፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ ወ.ዘ.ተ ሲነፈጉ ኖረዋል። ወያኔ በየዓመቱ መጀመሪያ ላይና በተለየዩያ ጊዜያት በትምህርት ስም የፖለቲካ ስራውን ለማካሄድ በሚያዘጋጃቸው ስብሰባዎች ላይ መምህራን የተለያዩ ሕጋዊ የመብት ጥያቄዎችን በማቅረባቸው ብቻ ተገድለዋል፣ ታሰረዋል፣ ከስራ ተፈናቅለዋል፣ የግዴታ ዝውውር ተፍጽሞባቸዋል፣ ለስደት ተደርገዋል፣ የወያኔ ዘረኛ ስርዓት ሰለባ ሆነው በገዛ አገራቸው እንደሁለተኛ ዜጋ ሊቆጠሩ በቅተዋል።ይህ በመምህራን ላይ የሚፈጸመው ዘርፈ ብዙ የግፍ ቀንበር ሊወርድ ካለበት ጊዜው ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው። መምህራንም ሆኑ ሌሎች ሲቢክ ማህበራት ያነሷቸው የመብት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙት የወያኔ ዘረኛና ገዳይ ስርዓት ተገርስሶ በምትኩ **<u>ሕዝባዊ ሥርዓት ሲቋቋም ብቻ ነው።</u>***

*ወያኔ በፍቅር ፣ በመተሳሰብ፣በኢትዮጵያዊነት ክር ተሰስረው የኖሩትን የኢትዮጵያን ብሔረሰቦች አንዱን ካንዱ ጋር በማጋጨት ማለትም ኦሮሞውን ከአማራ፣ ኦሮሞውን ከሲዳማ፣ ሲዳማውን ከወላይታ፣ ኦሮሞውን ከኢትዮጵያ ሱማሌ፣ አማራውን ከቅማንት ወ.ዘ.ተ ጋር ከፋፍሎ በማጣላት ለ26 ዓመታት በስልጣን ላይ ሊቆይ በቅቷል።አፍና ቅብቅብ ሁሌ አያበላም ሆነና ይኸው ዛሬ የወያኔ የከፋፍለህ ግዛ-ፖሊሲ ሊቀጥል አልቻለም ፤ አይችልምም። ይህን የወያኔ ሰይጣናዊ ተንኮል ሕዝቡ ተረድቶታል ። ወያኔ ለ26 ዓመታት የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን እርስ በርስ በማጋጨትና የዘረኝነትን እሳት በመጫር ፣ ደም በማፋሰስ ከዳር ሆኖ እሳቱን ሲሞቅ ከርሟል።*

*ከእንግዲህ የጫረው እሳት አየለበለበው ነው ። ሎጋው-ሎጋው ሽቦዬ ወያኔን የጫረው እሳት ሲፈጀው ታየ ሆኗል ነገሩ። ዶሮ ጭራ ጭራ መታረጃውን ታወጣለች እንዲሉ ወያኔም የጫረው የጎሳ ፖለቲካ ራሱን ይዞት ሊጠፋ አንድ ሐሙስ ነው የቀረው። በወያኔ መሰሪ ድርጊትና የዘር ፖለቲካ ሳቢያ በቅርቡ በጅጅጋ፣ በአጠቃላይ በሐረር የተለያዩ ቦታዎች ፣በኢሉባቦር በቡኖ በዳሌ በጮራ ወረዳ ቦሮ ከተማና በቤንሻንጉል ሕይወታቸውን እንዲያጡ ፣ እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ በብዙ መቶ ሺዎች አንዲፈናቀሉ የተደረገበትን፣ እንዲሁም ከቀናት በፊት በአምቦ ከተማ በአጋዚ ጦር በግፍ የተገደሉትን 10 እና ከ 20 በላይ ኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰባቸውን የመቁሰል አደጋ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ በጥብቅ ይኮንናል ፤ ያወግዛል። የተሰማውንም ጥልቅ ሀዘን ይገልጻል። ለቤተሰቦቻቸውም እግዚአብሔር ጽናቱን ይስጣችሁ ይላል።*

*በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ ቦታዎች የሚታዩት ሕዝባዊ እምቢተኝነት ትግል ከግብ ለማድረስ አገራዊ ቅርፅ እንዲይዝ ማድረጉ ትግሉ ግቡን እንዲመታና የድሉን ዋስትና ለማረጋገጥ ብቸኛ መንገድ ነው። የኢትዮጵያ መምህራን በ1966 ዓ.ም ለፈነዳው አብዮት ያደረጉትን ተጋድሎ ዛሬም በወያኔ ላይ መድገም ይኖርባቸዋል። ታሪካዊ ግዴታቸውም ነው። ከተማሪዎቻቸው ጋር በመሆን አሁን እየተቀጣጠለ ያለውን ሕዝባዊ ትግል መቀላቀል ፣ መደገፍ፣ ያላቸውን የድርጅት ልምድ በመጠቀም ትግሉን አቅጣጫ ማስያዝ፣ አገር-አቀፋዊ ቅርፅ እንዲይዝ የማድረግ ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል። የዘመናት የመብት ጥያቄዎች እንዲመለሱ መምህራን የግንኙነት መረብ በመፍጠር አጠቃላይ አገር አቀፍ የስራ ማቆም አድማ በመጥራት ሕዝባዊ ትግሉ ይበልጥ ጉልበት እንዲያገኝ እንዲያደርጉትና ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እንዲታገሉ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪውን ያቀርባል፣ ለተግባራዊነቱም የራሱን አስተዋፆ ያደርጋል።*

*የመምህራን መብት የሚከበረው የወያኔ ዘረኛ ስርዓት ሲገረሰስ ነው!*
*የተጀመረው ሕዝባዊ ትግል ይፋፋም!*
*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!*